፬ኛ ዓመት ቁጥር ፮
4th Year No. 6

ሐረር ኅዳር 14/1991
Harar Nov 23/1998

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

**HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE**

| ያንዱ ዋጋ 1፡00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 12/1991 ዓ.ም
በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረሪ ቋንቋ አካዳሚን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 12/1991 ዓ.ም------------------------------------------------------------ገጽ 83

## አዋጅ ቁጥር 12/1991 ዓ.ም

## በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረሪ ቋንቋ አካዳሚን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 12/1991

ከዘጠኙ የፌደራል ክልላዊ መንግሥታት አንዱ በሆነው በሐረሪ ሕዝብ ክልል የሐረሪ ቋንቋ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲሰራበት በመደንገጉ፣

ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግና ቋንቋውን ካለበት ደረጃ ከፍ በማድረግ፣ የሕዝቡ የባሕል የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማሕበራዊ እንቅስቃሴ መግለጫ እንዲሆን ለማድረግ

በቋንቋው ላይ ተከታታይ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ፣ ረቂቅ ፖሊሲዎችን የሚያዘጋጅ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ በፍትህ አካላትና በሌሎችም መስኮች የቋንቋው ግልጋሎት

ወጥነት ያለው አጠቃቀም እንዲኖረው የሚያስችል ተቋም በማስፈለጉ፣

የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሐረሪ ቋንቋ አካዳሚ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1/ አጭር ርዕስ

**13/ ቁጠሪነት**

1/ የአካዳሚው ተጠሪነት ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ይሆናል።

2/ የቦርዱ ሊቀመንበር ተጠሪነት ለጉባኤው ይሆናል።

3/ የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለቦርዱና ለጉባኤው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

4/ የካውንስሉ ተጠሪነት ለአካዳሚው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**14 ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊው ደንብ በቦርዱ ረቂ ከተዘጋጀ በኋላ በጉባኤው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጸድቆ ይወጣል።

**15/ ቅጣት**

ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት ይቀጣል።

**16/ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፤ መንግሥታዊ ድርጅት ወይንም የፖለቲካ ፓርቲ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

**17/ ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚፃረር ማንኛውም ሕግ ይህን አዋጅ በተመለከተ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የለውም።

**18/ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ኅዳር 14 ቀን 1991 ዓ.ም

ሐረር

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት

ፕሬዝዳንት